DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የቤተሰብ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**የቀደመ-መነሻ (Background)**
በዲሲ ካንውስል (DC Council)፣ ‘ዲሰሌክሲአ/Dyslexia’ እና ሌላ የማንበብ ችግሮች ላይ ምላሽ-የመስጠት ድንጋጌ - 2020፣ በጠቀሰው-ምክንያት፤ የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች - ‘RAN (Rapid Automatized Naming)’ን፣ ከትምህርት-ዓመት 2023-24 ጀምሮ፣ በቅድመ ማንበብና-መፃፍ ግምገማዎች ውስጥ ጨምሯል። መዋዕለሕፃናቶች እና የአንደኛ-ክፍል ተማሪዎች - በተቀናጀው የክፍል-ደረጃቸው ውስጥ በጣም-ዝቅተኛ ያስመዘገቡ እና ከመነሻ-ደረጃው (benchmark) በ‘RAN’ በጣም-ዝቅተኛ ያስመዘገቡ-ተማሪዎች፤ በንባብ ችግሮች (reading difficulties) - በ“ስጋት-ላይ/at risk” በሚል-ተለይተዋል። ይህ፣ ከ‘ዲሰሌክሲአ (dyslexia)’ ጋር ተዛማጅ-የሆኑ ችግሮችን፣ ሊያካትት ይችላል። የንባብ ችግሮች - ‘በስጋት-ላይ (at risk)’ ተብሎ-መለየት፤ በንባብ-ችግር የሕክምና-ምርመራ ውጤት ኣይደለም።

**ልጄ፤ “በስጋት-ላይ/at risk” ከሆነ/ነች፤ ‘ዲሰሌክሲአ (dyslexia)’ አላቸው-ማለት ነው?**
በግድ-ይህ ይሆናል-ማለት አይደለም። ልጃችሁ የምልከታ-ምርመራ-በተደረገ ጊዜ፣ በንባብ እድገት በማሳየት ላይ ችግሮች እንደታዩ ወይም ለ‘ዲሰሌክሲአ (dyslexia)’ “በስጋር-ላይ/at risk” እንደሆነ/ች የምልከታ-ምርመራ ተደርጓል። ብዙ ተማሪዎች፣ ከፍተኛ-ጥራት ካለው ለሁሉም-ክፍል ከሚሰጠው የትምህርት-አሰጣጥ በተጨማሪ፤ በአነስተኛ ቡድን-በሚሰጠው የትምህርት-አሰጣጥ - በፍጥነት እና በአዎንታዊነት ምላሽ-የሚሰጡ እና “በስጋር-ላይ/at risk” ምድባቸውም ይወጣሉ።

**“በስጋት-ላይ/at risk” ነው/ች ማለት፤ ልጄ የንባብ እክል አለበት/ባት ማለት ነው?**
በግድ-ይህ ይሆናል-ማለት አይደለም። “በስጋር-ላይ/at risk” ማለት፤ በክፍል-ደረጃቸው የሚጠበቅባቸው ላይ ለመድረስ፣ ተጨማሪ የማንበብ ትምህርት-አሰጣጥ ሊያስፈልጋቸው ይችላል-ማለት ነው። ተማሪዎች የተዋቀረ የማንበብና-መፃፍ ጣልቃ-ገብነትን እያገኙ ከሆነ እና ለውጥ-እያመጡ ካልሆነ፤ የትምህርት ቤቱ ‘MTSS’ (ባለብዙ-ዘርፍ የእርዳታዎች ዘዴ/multi-tiered systems of support) ቡድን፤ ተጨማሪ-እርዳታዎችን እና ቀጣይ-እርምጃዎችን ይፈልጋል።

**በመኖሪያ-ቤት ውስጥ፣ ምን ላደርግ እችላለሁ?**
እንደ ወላጅነታችሁ ወይም እንደ እንክብካቤ-ሰጪነታችሁ፤ ለልጃችሁ በመኖሪያ-ቤት ውስጥ ልትሰጧቸው የምትችሉት በጣም ቀልጣፋና-በስራ ላይ የሚውል እርዳታ - ከልጃችሁ ጋር-ሆናችሁ ማንበብ-ነው። ልጃችሁ፤ ራሱን-ችሎ በራሱ-ማንበብ እስካሁን-ካልጀመረ/ረች፣ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ (read aloud)ን ልታደርጉላቸው ትችላላችሁ። እንደ-ቤተሰብ ሆናችሁ፤ በድምጽ-የሚነበቡትን መጽሐፍት (audiobooks)ን ማዳመጥም-ትችላላችሁ። ልጃችሁ፤ በራሳቸው ማንበብ ከጀመሩ፣ በአስተማሪው የተመከረውን - ‘decodable text’ ከቀላል የቃል ፓተርኖች (patterns) ጋር፣ ተጠቀሙ። ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት እየመጡ - እነዚህን የቅድመ-ማንበብና መፃፍ ችሎታዎች (early literacy skills) ከአስተማሪዎቻቸው መማር-መቻላቸውም፣ በጣም አስፈላጊ-ነው።

**ስለ ቅድመ-ማንበብና መፃፍ (early literacy) የበለጠ ከየት-ማወቅ እችላለሁ፤ እና እንዴት ልጄን መርዳት እችላለሁ?**
www.readingrockets.com፣ ለቤተሰቦች - በርካታ ጽሁፎችን እና ቪዲዮችን ይዟል

**የልጄን አስተማሪ፣ ምን መጠየቅ አለብኝ?**
1. የልጄ - የማንበብ ጠንካራ-ጎኖች እና ደካማ-ጎኖች ምን-ምን ናቸው?
2. በ‘DIBELS (Dynamic Indicators of Basic Early Literacy Skills)’ ልጄ - እንዴት-ሰርቷል?
3. የልጄን የማንባብ እድገት ላይ ለመርዳት፣ ምን እያደረጋችሁ ነው?
4. ልጄ እድገት እያመጣ መሆኑን እንዴት ማወቅ እንችላለን?

**ልጄ፤ ከክፍል-ጓደኞቼ በተለየ-ሁኔታ የትምህርት-አሰጣጥን ያገኛል/ታገኛለች?**
በየዕለቱ ከሚሰጠው የሙሉ-ክፍል (whole class) የትምህርት-አሰጣጥ በተጨማሪ፤ ለእነርሱ-ብቻ በተቀረጸ እና የንባብ-ፍላጎታቸው ላይ ያተኮረ የትምህርት-አሰጣጥን ልጃችሁ ያገኛል። አብዛኛዎቹ ተማሪዎች፣ ይህን ማስተማር - በመማሪያክፍላቸው ውስጥ ከአስተማሪያቸው ጋር ሆነው፣ በየዕለታዊው የአነስተኛ ቡድን (daily small group) የንባብ-ጊዜ ውስጥ፣ ትምህርቱን ያገኛሉ። አንዳንድ ተማሪዎች፣ የትምህርት-አሰጣጡን ከመማሪያክፍላቸው ውጪ ያገኛሉ። የትምህርት ቤቱ የ‘MTSS’ ቡድን - (ባለብዙ-ዘርፍ የእርዳታዎች ዘዴ ቡድን)፣ እነዚህን-ምርጫዎች ያደርጋሉ። ተማሪዎች፤ ማንኛውንም - ዋና የመማሪያ ጊዜን የሚያጡ/የሚያመልጣቸው ኣይሆንም።

**እኔ-በልጅነቴ በንባብ-ላይ እቸገር ነበር (ወይም በቤተሰቤ የሚገኝ ሰው - ይቸገር-ነበር)፣ ይህ ማለት-ልጄ እንደዚሁ ችግር-ይገጥመዋል ማለት ነው?**
‘ዲሰሌክሲአ (Dyslexia)’፣ በአንጎል-አቀማመጥ ላይ በሚኖር ልዩነቶች የሚፈጠር እና በዘር-የሚወራረስ/ጀኔቲክ (genetic) ነው። ይህም ማለት፤ ተማሪዎች ‘ዲሰሌክሲአ (dyslexia)’ን ከቤተሰብ-አባላቶች ሊወርሱት ይችላሉ። ንባብን በመማር ተቸግራችሁ ከነበረ፣ ልጃችሁ 50% የበለጠ እርሱም/እርሷም በንባብ ሊቸገሩ የሚችሉበት ሁኔታ አለ።

DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

**ልጄ፣ በ‘PreK’ ጥሩ ሰርቷል/ታለች፤ አሁን ለምንድነው “በስጋት-ላይ/at risk” የሆኑት?**

በቀድመ ማንባብና መፃፍ (early literacy) የምልከታ-ምርመራ ማድረግ የሚረዳን፣ በኋላ-ላይ ለንባብ በሚያስፈልጋቸው ችሎታዎች ላይ - እንደ በቃላቶች ላይ ትንሿን ድምጽ እንደማዳመጥ-ያሉትን ችሎታዎች ላይ አስቸጋሪ ጊዜ/a hard time እየገጠማቸው ያሉትን ተማሪዎች ፈልጎ-ለማግኘት ነው። ይህን የምልከታ-ምርመራ በመዋዕለሕፃናት የምንጀምር-ሲሆን፤ ይህም የሆነበት ምክንያት - ይህ ጊዜ እነዚህን ችሎታዎች ማስተማር የምንጀምርበት እና የትኞቹ-ተማሪዎች ተጨማሪ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ለማወቅ-ነው።

**ለምንድነው-ይህ በዓመቱ-መጀመሪያ ላይ የተሰጠው?**

የንባብ ችግሮች እንዳላቸውና በስጋት-ላይ/at risk የሆኑ-ተማሪዎች፣ በቅድሚያ-የተጀመረ - ለንባብ-ችሎታዎች ላይ በሚያስፈልጋቸው-ነገሮች ላይ፣ የማስተማር-እርዳታን በማግኘታቸው የበለጠ-የተሻለ-ይሰራሉ። በማንበብ-ጠንካራ ሆነው በመማሪያ-ክፍላቸው በትክክለኛው-ደረጃ ላይ እንዲሆኑ ለማድረግ ሲባል፤ ወዲያውኑ-የትኞቹ ተማሪዎች ተጨማሪ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል የሚለውን ፈልገን-ማግኘት እንፈልጋለን።

**የልጄን የዕድገት ሂደት - ትምህርት ቤቱ እንዴት-ነው ሊከታተል የሚችለው?**

“በስጋር-ላይ/at risk” ለሚገኙ ተማሪዎች - በቅድመ ማንባብና-መፃፍ ችሎታዎች ላይ እድገት-እያሳዩ እንደሆነ ለማየት፣ የ1-ደቂቃ ፈተና በየ2-ሣምንታቶች ይሰጣቸዋል። አስተማሪዎች፣ የትምህርት ቤት አመራሮች፣ እና የ‘MTSS’ ቡድን፤ በእነዚህ የፈተና ውጤቶች ላይ በየ2 ሣምንታቱ ይመለከቱ እና፣ ማን-እያደገ እንደሆነ እና ማን የበለጠ እርዳታ-እንደሚያስፈልገው ይመለከታሉ። በክፍል-ደረጃው የሚጠበቀውን፣ የመነሻ-ደረጃዎች (benchmarks)ን እስከሚያሟሉ ድረስ፣ ለተማሪዎች ክትትል-ማድረጋችንን እንቀጥላለን።

**ልጄ፣ ይህን ምርመራ/test እንደገና መውሰድ ይችላል?**

የቅድመ-ማንበብና መፃፍ (The early literacy) የምርመራ-ምልከታ ማድረጊያው፤ ከK-2 ውስጥ ላሉ ተማሪዎች - በዓመት ሦስት ጊዜ በሚከተሉትን-ወራት ይሰጣል: ሴፕቴምበር (September)፣ ጄንዋሪ (January) እና በጁን (June) ውስጥ - ይሰጣል። በእያንዳንዱ የመፈተኛ ክፍት-ጊዜ (testing window) ወቅት፣ ተማሪው ከ“በስጋር-ላይ/at risk” ከሚለው ምድብ ወደሌላ ሊገባ ይችላል። ተማሪዎች፣ ‘RAN’ን የሚወስዱት፤ በዓመቱ-መጀመሪያ ላይ በመዋዕለሕፃናት እና በአንደኛ-ክፍል ብቻ-ነው።

**ይህ ማለት - ልጄ፣ በየግል-የተዘጋጀ የትምህርት ዕቅድ (individualized education plan (IEP) - ያስፈልገዋል/ጋታል ወይም ብቁነትን አግኝተዋል ማለት-ነው?**

የለም/No፤ ‘DIBELS’ እና ‘RAN’ ለዚህ ስጋት/risk መመርመሪያዎች-ናቸው። የጉዳተኝነት (disability) የሕክምና-ውጤትን የማይሰጥ፤ ወይም-ደግሞ ተማሪዎች ጉዳተኝነት-አላቸው ብለን-እንድናውቅ - በበቂ-ሁኔታ የሚያሳውቀን ነገር የለም። ተማሪው በሚሰጠው-ተጨማሪ እርዳታ በመማሪያክፍሉ ውስጥ ዕድገትን-ካላሳየ፤ በትምህርት ቤቱ የሚገኝ የ‘MTSS’ ቡድን፣ ተጨማሪ እርዳታን በቦታው-የሚያስቀምጥ እና ‘IEP’ን ከግምት-ውስጥ ማስገባት ማስፈለጉን ያሰቡበት-ነገር እንደሆነ ለማወቅ ቤተሰቦችን ያነጋግራሉ።

**በአሁኑ-ጊዜ ልጄ ባለው ጉዳተኝነት ምክንያት - ካለው ‘IEP’ ጋር፣ ይህ እንዴት ይቀናጃል?**

ልጃችሁ - በግል-የተዘጋጀ የትምህርት ዕቅድ (individualized education plan (IEP) አስቀድሞውኑ-የነበረው ከሆነ፤ ለሁሉም-ተማሪዎች ከሚሰጠው የትምህርት-አሰጣጥ እርዳታዎች ጋር - ተማሪዎች፣ ተጨማሪ-ሆኖ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች (special education services)ን የሚያገኙ-እንጂ፣ እርሱን በመተካት - እንዳልሆነ፤ እባካችሁ አስታውሱ። ማንኛውንም-ጥያቄዎች፤ ወደ ልጃችሁን የልዩ ትምህርት ጉዳይ-አስፈፃሚ (special education case manager) - በማቅረብ - መጠየቅ-ትችላላችሁ።

**ልጄ ባለብዙ-ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪ ከሆነ፣ ይህ ምን-ማለት ነው?**

ልጃችሁ - እንደ የእንግሊዘኛ-ቋንቋን የሚማር (English Learner)/ባለብዙ ቋንቋ ተማሪ (Multilingual Learner) ሆኖ - የESOL (የእንግሊዘኛ-ቋንቋ፣ ሌላ-ቋንቋዎችን ለሚናገሩ/English for Speakers of Other Languages) አገልግሎቶች-ውስጥ ተለይቶ-የታወቀ ከሆነ፤ የምልከታ-ምርመራ ውጤታቸው - እያደገ ከሚመጣው የእንግሊዘኛ-ቋንቋቸው ጋር በተያያዘ ሊታይ የሚችል እና፣ የማንበብና-መፃፍ እድገታቸውን - ይህን-በአዕምሮአችን በማስቀመጥ - መከታተላችንን-እንቀጥላለን።

ሌላ ጥያቄዎች ካሏችሁ፣ እባካችሁ - የልጃችሁን አስተማሪ ጠይቁ ወይም በliteracyscreening@k12.dc.gov. ኢሜል አድርጉ።